# ጮክ ብሎ የማንበብ መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental. until every child reads




## ፊየስታ፤ ሲየስታ (Siesta)

ደራሲ፤ ጂንጀር ፎግለስ ጋይ (Ginger Foglesong Guy)
ሰዓሊ፤ ሬኔ ኪንግ ሞሬኖ (Rene King Moreno)
ይዘቶች (**Themes**)፤ ፋሚሊ (Family) ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ (Bilingual)
የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (**Book Brief**)፤ ይህ አስደሳች የስዕል መጽሐፍ ቀላል ቃላትን ለማስተማር ሁለቱንም ስፓኒሽ እና እንግሊዝኛ ይጠቀማል። ወደመኝታ የሚጓቸውን ጊዜ ለማዘግየት ያላቸውን ትልቅ ምናብ ስለሚጠቀሙ ሁለት ልጆች ተጫዋች ታሪክ ይነግረናል!

## ጮክ ብለው ያንብቡ

ከንባብ በፊት፤ ዳራ ይገንቡ (**Build Background)**

- "ትንሽ ከማሸለብ ወይም ከመተኛት በፊት ምን ማድረግ ትወዳለህ? ልዩ የዕለት ተዕለት ተግባር አለህ?" በማለት ይጠይቁ።

በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

- ልጆቹ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? በትክክል ለመተኛት ይሄዳሉ?
- ለምንድነው ልጆቹ ከማሸለብ ይልቅ መጫወታቸውን የሚቀጥሉት? ምን አስደሳች ነገሮች ያደርጋሉ?
- ልጆቹ በመጨረሻ ለሲየስታ (siesta) እንዴት ይዘጋጃሉ?
- በሁለቱም በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ ምን ቃላቶችን ሰሙ?

ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ

- "በታሪኩ ውስጥ ምን ተከሰተ? ልጆቹ በመጨረሻ የሚተኙት ለምን ይመስልሃል? ካደረጉት ነገሮች የወደድከው የትኛውን ነው?" በማለት ይጠይቁ።

## ተዛማጅ ተግባራት

ልጅዎ ይህንን መጽሃፍ ከወደደው፤

- ታሪኩን ይተግብሩ! ከመተኛት በፊት ልጆቹ ያከናወኗቸውን ተግባራት አስመስለው ይተግብሩ። ሲጫወቱ ቀላል ስፓኒሽ እና እንግሊዝኛ ቃላትን ይጠቀሙ፤ ልክ በታሪኩ ውስጥ እንዳሉ ልጆች።
- አዲስ ቃላትን በሁለቱም በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ ከመጽሐፉ አንድ ላይ መናገርን ተለማመዱ።
- በቀላል የስፓኒሽ እና የእንግሊዝኛ ቃላት፣ የማሸለብ ጊዜ ታሪኮች ወይም የሚያስደስቱ ታሪኮች ላይ የተጻፉ ተጨማሪ መጽሃፎችን ያንብቡ።


©2026 Reading Is Fundamental